# FGM
# አካልሽ የአንቺ ነው።

SAFETY, TRUST AND RESPECT
DIOGELWCH, YMDDIRIED A PHARCH



FGM የሴት ልጅ ግርዛትን ያመለክታል:: አንድ ግለሰብ ያለ ህክምና ምክንያት የሴት ልጅን ሃፍረተ ስጋን ሁሉ ወይም በከፊል ሲቆርጥ ወይም ሲያስወግድ ነው። እንዲሁም ‘መቁረጥ’ ወይም ‘የሴቶች ግርዛት’ በመባልም ይታወቃል ፡፡ የተለያዩ “የመቁረጥ” ደረጃዎች ሲኖሩ ነገር ግን እያንዳንዱ ስቃይ፣ ንዴት እንዲሁም ከፍተኛ፣ የረጅም ጊዜ ህይወት የአካላዊ እና ስነልቦና ተፅዕኖ ይኖረዋል።

ልጃገረዶች FGM ከእፍረት ወይም ከመዋረድ “እንደሚጠብቅ” እንዲሁም መቆረጥ ደስተኛ ህይወት እንዲኖራቸው እንደሚረዳ ምናልባት ሊነገራቸው ይችላል። ምክንያቱ ምንም ይሁን፣ FGM ጥቃት ነው እንዲሁም ሁልጊዜ ስህተት ነው።

በትክክል በሰውነትሽ ውስጥ ምንም የሚያሳፍርም ነገር የለም ፡፡ እንደዚ ነው የተፈጠርሽው።

በአላስፈላጊ ህመም ውስጥ ማለፍ አለመፈለግዋ መዋረድ ማለት አይደለም።

ጥቃት እና ኀይለኛነት በጭራሽ መበረታታት የለበትም እንዲሁም ለደስተኝነት አስተዋፅዎ የለውም።

**ሁሉም የFGM አይነቶች ጥቃት ናቸው፣ እንዲሁም በዩናይትድ ኪንግደም(እንግሊዝ) ሕገወጥ ተግባር ነው።**

**ማንኛውም ሰው ደህንነቱ የመጠበቅ ፣ የመከለል ፣ከፍርሃትና ጉዳት የመጠበቅ መብት አለው፣ በተለይ ከምንወዳቸው እና እንወዳችዋለን ከሚሉን።**

**FGM ደርሶብሽ ከሆነ ወይም አደጋ ላይ እንደሆንሽ ስጋት ካደረብሽ፣**

**በማንኛውም ጊዜ እርዳታ ማግኘት ትችያለሽ! ብቻሽን አይደለሽም።**

## FGM ደርሶብሻል?

### እርዳታ እና እገዛ

**የNSPCCን አማካሪ ለማነጋገሪ**

**ደውዪ 0800 028 3550 (FGM የእገዛ ስልክ መስመር 24/7)**
**ኢሜል fgmhelp@nspcc.org.uk**
**ወይም ለ1-2-1 ለኢንተርኔት ፅሁፍ ንግግር ድህረገፃቸውን ጎብኚ**

**ምን እርምጃ መውሰድ እንዳለብሽ፣ በተጨማሪም የት ድጋፍ ማግኘት እንደምትችዪ ሊያነጋግሩሽ ይችላሉ።**

**ህመም እየተሰማሽ ከሆነ ወይም ጥሩ ስሜት ካልተሰማሽ፣ የሕክምና ዕርዳታ ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው።**
**ለሐኪምሽ መደወል ትችያለሽ፣ ወይም ምን ማድረግ እንዳለብሽ እርግጠኛ ካልሆንሽ፣ 24/7**
**የNHS 111 ዌልስ የእርዳታ ስልክ መስመር በ111 ወይም 0845 46 47 ለመደወል ሞክሪ።**

**ለድንገተኛ ጊዜ፣ 999 ደውዪ።**

## FGM በአንቺ ወይም በምታውቂያት ልጅ ላይ ሊከሰት ይችላል ብለሽ ትጨነቂያለሽ?

**በFGM ምክንያት ስሜትሽ ጫና ሊሰማው ይችላል። ካልተቆረጥሽ፣ ቤተሰቤ ያዝኑብኝ ይሆናል ብለሽ ልትጨነቂ ትችያሽ። ምናልባት የቤተሰብሽ ክብር በዚህ ላይ እንደሚመሰረት ተነግሮሽ ይሆናል። ይህ ትክክል አይደለም።**

**FGM በጭራሽ ትክክል አይደለም። ጥቃት ነው።**
**ደህንነትሽን የመጠበቅ እና ድጋፍ የማግኘት መብት አለሽ።**

**መጨነቅሽን ለሰው መንገር አስፈሪ ሊሆን ይችላል። ምናልባት ወላጆቼ ችግር ውስጥ ይገቡ ይሆን፣ ወይም ቤተሰቤ እና ማህበረሰቡ ይቃወሙኛል ብለሽ ትጨነቂ ይሆናል።**
**እንዲህ ዓይነቱ ስሜት የተለመደ ነገር ነው።**

**ምክር እና ድጋፍ እንዴት ማግኘት እንደምትችዪ ከዚህ በታች ተመልከቺ።**




**NSPCC - የFGM የእርዳታ ስልክ መስመር - 0800 028 3550** – ኢሜል **fgmhelp@nspcc.org.uk** - 1-2-1 ለኢንተርኔት ፅሁፍ ንግግር **እዚህ ጋር** ይጫኑ
**BAWSO - 0800 731 8147** - በዌልስ ውስጥ ለጥቁር እና ለአናሳ ብሔር ሰዎች መረጃ፣ ምክር እና ድጋፍ።
**Daughters of Eve (የሄዋን ልጆች) - ለፅሁፍ መልዕክት 07983 030 488** - የFGM ተግባር ከሚፈጽሙ ማህበረሰቦች የወጣቶችን አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ ፣ ፆታዊ እና የስነ-ተዋልዶ ጤና መብቶችን ለመጠበቅ ይሠራል። **ድህረገፃቸውን** ይጎብኙ።
**Petals** - ስለ FGM መረጃን የያዘ የወጣቶች መተግበሪያን ያውርዱ **ከዚህ**።
**ሁላችንም ያገባናል (Everybody's Business) –** በወጣቶች የሚመራ ለወጣቶች የFGM መረጃ ድህረገጽ። **ይህን** ይጎብኙ።

Live Fear Free Helpline
Llinell Gymorth Byw Heb Ofn
0808 80 10 800

Cymorth i Ferched Cymru
Welsh Women's Aid

# የግዳጅ ጋብቻ

S.T.A.R
SAFETY, TRUST AND RESPECT
DIOGELWCH, YMDDIRIED A PHARCH



ሁለት ሰዎች የሚዋደዱ ከሆነ፣ ጋብቻ ለመመስረት ይመርጡ ይሆናል። በማንኛውም ጋብቻ፣ ሁለቱም ተጣማሪዎች ጋብቻ ለመመስረት መፈለግ እና መስማማት አለባቸው ::

**ማንም የማይፈልገውን ሰው ጋር ጋብቻ ለመመስረት መገደድ የለበትም :: ስህተት እና ህግን የሚጻረር ነው።**

አንዳንድ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ጋብቻ እንዲመሰርቱ የሚያስገድዷቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ፣ ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ትውፊቶች፣ በቤተሰብ ውስጥ ስላለ ዝና እና ክብር ስጋት፣ ገንዘብ፣ ልጃቸው ሌዝቢያን በመሆኗ ተቀባይነት ማጣት፣ ግብረ-ሰዶማዊነት፣ ወይም ከማንኛውም ፆታ ጋር የሚኖር ግንኙነትን ያካትታል፣ ልጆቻቸው ግንኙነቶች ወይም ወሲብ እንዲፈፅሙ እንዲሁም በማህበረሰቡ ወይም በሌሎች የቤተሰብ አባላት ግፊት እንዲደረግባቸው አይፈልጉም፣ :: ምናልባት ለእርስዎ በጣም ጥሩ እንደሆነ ያምናሉ።

**ከነዚህ ምክንያቶች ውስጥ አንዳቸውም ትክክል አይደሉም ::**

## የታቀደ ጋብቻ

አንዳንድ ጊዜ፣ ሁለት ቤተሰቦች ልጆቻቸው ለጋብቻ እዕድሜቸው ሲደርስ እንዲጋቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ። ሁለቱም ተጣማሪዎች አንዳቸው ሌላውን ለማግባት እና ጋብቻ ለመመስረት እስከተስማሙ ድረስ ይህ መልካም ነው።

**አዎ፣ እፈፅማለሁ!**
(ጋብቻ ለመመስረት ይፈልጋሉ)

## የግዳጅ ጋብቻ

ይህ የተለየ ነው :: አንዱ ወይም ሁለቱም ተጣማሪዎች ያለፍላጎታቸው ጋብቻ እንዲመሰርቱ በሚገደዱበት ጊዜ ነው :: ወላጆችዎ **'አይሆንም' የማለት መብትዎን** ካላከበሩ የታቀደው ጋብቻ የግዳጅ ጋብቻ ይሆናል።
እንዲሁም ከተጣማሪዎቹ አንዱ አለመስማማቱን ለመግለፅ በማይችልበት ጊዜ ጋብቻው “የግዳጅ” ይሆናል።
(ለምሳሌ ከ16 ዓመት በታች የሆነ ልጅ፣ ወይም የመማር ውስንነት ያለበት አዋቂ ሰው)

**ምርጫ የለኝም**

ወላጆችዎን ሊወዱ ይችላሉ፣ ነገር ግን በግዳጅ ጋብቻ ሲመሰርቱ ሊናደዱ፣ ሊረበሹ እና የድብርት ስሜት ሊሰማዎት ይችላል :: ጋብቻ ካልመሰረቱ በቤተሰብዎ ላይ ውርደት እንደሚያመጡ ነግረዎት ሊሆን ይችላል :: ምናልባትም እንደሚከዱሽ ነግረውሽ ወይም በሃይል አስፈራርተው ይሆናል ::

**ይህ ጥቃት ነው።**

**የሆነ ሰው ጋር የግዳጅ ጋብቻ እንዲፈፅሙ ተገድጃለሁ ብለው ተጨንቀዋል?**

**ያልመረጡት ጋብቻ እንደ ወጥመድ ሆኖ ይሰማዎታል?**

**እርዳታ ማግኘት ይችላሉ!**




**NSPCC የልጆች የስልክ መስመር- 0800 11 11** - 1-2-1 ለኢንተርኔት ፅሁፍ ንግግር **እዚህ ጋር**።
**BAWSO - 0800 731 8147 - በዌልስ ውስጥ ለBME ሰዎች መረጃ፣ ምክር እና ድጋፍ።**
**ከፍርሃት ነፃ ኑሮ (Live Fear Free) - 0808 80 10 800 (ስልክ) - 0786 00 77 333 (ለፅሁፍ መልዕክት) - በኢንተርኔት ፅሁፍ ንግግር**
**የግዳጅ ጋብቻ መምሪያ - 020 7008 0151 - fmu@fco.gov.uk - በዚህ** ድህረገፁን ያገናኙ።
**Karma Nirvana - 0800 5999 247 - በዚህ** ድህረገፁን ያገናኙ።

**ሕይወትዎ አደጋ ላይ ነው ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ 999 ይደውሉ :: የግዳጅ ጋብቻ እንዲፈፅሙ ከሀገር ውጭ እወሰዳለሁ ብለው ካሰቡ፣ የግዳጅ ጋብቻ መምሪያን ወይም በልጆች ስልክ መስመርን ያነጋግሩ።**

**በእንግሊዝ ሀገር ውስጥ፣ ከ16 ዓመት በታች ከሆኑና ጋብቻ እንዲፈፅሙ ጫና ከተደረገብዎ፣ ይህ የልጆች ጋብቻ እና ህገወጥ ነው።**

Live Fear Free Helpline
Llinell Gymorth Byw Heb Ofn
0808 80 10 800

S.T.A.R

Cymorth i Ferched Cymru
Welsh Women's Aid